# የሲያትል ቅድመ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ግምገማ 2024

የ Seattle Preschool Program (SPP) በከተማው ውስጥ የ 3- እና የ 4-አመት ህጻናትን ያገለግላል፤ ይህም ከመማሪያ ክፍሎች ጋር በማህበረሰብ ላይ በተመሰረቱ ድርጅቶች፣ የቤተሰብ ህጻናት እንክብካቤ እና የ Seattle Public Schools (SPS) ጋር በመተባበር ያደርገዋል። SPP በመዋዕለ ህጻናት ዝግጁነት ላይ ያሉ የእድል ክፍተቶችን ለማስወገድ እና ከፍተኛ ጥራት ያለው የቅድመ ትምህርት ፍትሃዊ ተደራሽነት ያለው ትምህርትን ለማቅረብ ያለመ ነው። የሲያትል የትምህርት እና የቅድመ ትምህርት ክፍል (DEEL) SPP ን ለመገምገም ከ Education Northwest ጋር በመተባበር ይሰራል። ይህ አጭር ከግምገማው የተመረጡ ግኝቶችን ያቀርባል (ለዝርዝሮቹ ሙሉውን ዘገባ ይመልከቱ)።

### የማህበረሰብ አስተያየት

ግምገማው ማህበረሰብ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን እና አመለካከቶችን የሚያንጸባርቅ መሆኑን ለማረጋገጥ፡ Education Northwest ከ SPP ቤተሰቦች፣ የማህበረሰብ አባላት፣ የፕሮግራም ዳይሬክተሮች እና አስተማሪዎች አማካሪ ኮሚቴ ጋር ይሰራል። አማካሪ ኮሚቴው ግምገማውን በመንደፍ፣ እርምጃዎችን እና ጥያቄዎችን በመገምገም እንዲሁም ግኝቶቹን በማዘጋጀት ጠቃሚ አጋር ነው።

## የግምገማ ውሂብ



ይህ ግምገማ ከተለያዩ ምንጮች የተገኘ መጠናዊ እና ጥራት ያለው መረጃን ተጠቅሟል፤ ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል:-

- **የዳሰሳ ጥናት ውሂብ።** የቤተሰብ ጥናቱ በግምት 2,060 ቤተሰቦች 1,056 ምላሽ ሰጪዎች ነበሩት፤ እንዲሁም 67% ምላሽ ሰጪዎች ጥቁሮች ሲሆኑ 32% የሚሆኑት ደግሞ በቤት ውስጥ ከእንግሊዝኛ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ናቸው። በአስተማሪው ዳሰሳ ላይ ከ 296 የ SPP መምህራን፡ 139 ምላሽ ሰጥተዋል፤ 64% የአስተማሪ ምላሽ ሰጪዎች ጥቁሮች ሲሆኑ፡ 25% የሚሆኑት ደግሞ ከእንግሊዝኛ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ናቸው።
- **የትኩረት ቡድኖች እና ቃለመጠይቆች።** የግምገማ ቡድኑ 15 የትኩረት ቡድኖችን እና ቃለ ምልልሶችን ከ SPP መምህራን (14 ከተለያዩ የሳይቶች አይነት መምህራን)፣ የ SPS መዋለ ህጻናት አስተማሪዎች (3 አስተማሪዎች)፣ አሰልጣኞች (6 አሰልጣኞች)፣ የ DEEL ሰራተኞች (8 ሰራተኞች)፣ እና የቤተሰብ አባላት (26፡ 19 ጥቁሮች እና 3 በስፓኒሽ የተሳተፉ የሚያጠቃላል) አካሄደዋል።
- **DEEL እና የዋሽንግተን ግዛት ውሂብ።** የግምገማው ቡድን ገላጭ ስታቲስቲክስን ለማስላት እና በተለያዩ የ SPP ገጽታዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመመርመር በ DEEL ልጆች፣ አስተማሪዎች እና ክፍሎች ላይ አስተዳደራዊ መረጃ ተጠቅሟል። የዋሽንግተን ስቴት መረጃ በ SPP ውስጥ ያሉ ልጆችን በዋሽንግተን ግዛት በገንዘብ በሚደገፈው የቅድመ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ከተመዘገቡ ተመሳሳይ ልጆች ጋር ለማነጻጸር እና የ SPP ተሳትፎ በኋለኛው የህጻናት ውጤቶች ላይ ያለውን ተጽእኖ ለመገመት ጥቅም ላይ ውሏል።[1]

# ስለ SPP ጥቅሞች እና ጥራት የቤተሰብ ግንዛቤ

## ቤተሰቦች በአጠቃላይ፣ የጥቁር ቤተሰቦች፣ እና የቋንቋ ልዩነት ያላቸው ቤተሰቦች ስለ SPP ብዙ ጥቅሞች ሪፖርት አድርገዋል

- የቤተሰብ አባላት በዳሰሳ ጥናቶች እና በትኩረት ቡድኖች ሪፖርት በሰጡት መሰረት፡ በ SPP ውስጥ በመሳተፋቸው ልጆቻቸው፡ ማህበራዊ-ስሜታዊ እና አካዳሚያዊ ክህሎቶችን እንዳገኙ እንዲሁም የጥቁር ቤተሰቦች ከነጭ ቤተሰቦች በመጠኑ ከፍ ባለ ደረጃ አወንታዊ ለውጦችን ሪፖርት አድርገዋል።
- በ SPP ያለው የአስተማሪዎች ልዩነት፡ በብዙ የጥቁር ቤተሰቦች እና የተለያየ ቋንቋ በሚናገሩ ቤተሰቦች እንደ የፕሮግራሙ ጥቅም ይታያል።
- ቤተሰቦች SPP የቅድመ ትምህርት ቤትን ዋጋ ተመጣጣኝ እንዲሆን እንደሚያግዝ እና አንዳንድ ቤተሰቦች ማህበረሰብ እንዲገነቡ እንደረዳቸው ይናገራሉ።

> *"ልጄ የመዋለ ሕጻናት ትምህርትን ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ በስሜታዊ እና በማህበራዊ ደረጃ አድጋለች።"*
>
> **- የ SPP የቤተሰብ አባል**

## ምንም እንኳን አተገባበሩ በብዙ አካባቢዎች እንዲሻሻል ቢያስፈልግም SPP ለአብዛኛዎቹ ልጆች እና ቤተሰቦች ከፍተኛ ጥራት ያለው ልምድ ያቀርባል



- ከ80 በመቶ በላይ ጥናት የተደረገባቸው ቤተሰቦች የልጃቸውን ቅድመ ትምህርት ቤት ከሚጠብቁት ከፍተኛ ጥራት ያለው ቅድመ ትምህርት ቤት አንድ አይነት መሆኑን ተስማምተዋል። ይህ የመቶኛ ቁጥር በጥቁር ቤተሰቦች፣ በቋንቋ የተለያዩ ቤተሰቦች፣ እና በግል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) የሚማር ልጅ ባላቸው ቤተሰቦች መካከል ተመሳሳይ ነበር።
- የክፍል ምዘና የውጤት አሰጣጥ ስርዓት (CLASS)  የ SPP ክፍልን ጥራት የሚለኩ ውጤቶች፡ ባለፈው አመት በክፍል አደረጃጀት በ3 ከመቶ፣ በስሜታዊ ድጋፍ 1.5 ከመቶ፣ እና 19 ከመቶ በትምህርታዊ ድጋፍ ጨምረዋል።
- Education Northwest የ SPP የምርጥ ትግበራ ዝርዝር ለማዘጋጀት ከ DEEL ጋር በመተባበር ሰርተዋል። ይህ የማረጋገጫ ዝርዝር እንደ አስፈላጊ ስርአተ ትምህርት መጠቀም፣ የመምህራን መመዘኛዎች፣ እና በሙያዊ እድገት መሳተፍን ያጠቃልላል። ምንም እንኳን የመማሪያ ክፍሎች በሁሉም ክፍሎች ላይ ጥሩ አተገባበር ባይኖራቸውም አብዛኛዎቹ የመማርያ ክፍሎች ግን ዋናዋና በሆኑ የ SPP ብዙ ነገሮች ላይ ጥሩ አተገባበር ነበራቸው። ለመሻሻል ቦታ ያላቸው ክፍሎች የመምህራን የማቀድ ጊዜ እና በአስፈላጊ ስልጠና ላይ መሳተፍን ያካትታሉ።

# የመዋዕለ ሕጻናት ዝግጁነት

## የማህበራዊ-ስሜታዊ ችሎታዎች ለመዋዕለ ሕጻናት ዝግጁነት ቁልፍ ናቸው፤ እንዲሁም አብዛኞቹ ቤተሰቦች ልጃቸው ለመዋዕለ ሕጻናት ዝግጁ እንደሆነ ሲያምኑ፡ አንዳንዶች ግን የግለሰብ ዝግጁነት በተመለከተ የበለጠ መረጃ ይፈልጋሉ

- አብዛኛዎቹ የ SPP መምህራን እና የ SPS መዋእለ ህጻናት መምህራን በዳሰሳ ጥናቶች እና በትኩረት ቡድኖች ውስጥ ማህበራዊ-ስሜታዊ ችሎታዎች፣ ራስን መቆጣጠርን ጨምሮ፣ ለመዋዕለ ህጻናት ዝግጁነት በጣም አስፈላጊ መሆናቸውን አጥብቀው ይገልጻሉ።
- አንዳንድ ቤተሰቦች እና የ SPS መዋእለ ህጻናት አስተማሪዎች በግል ልጆች ላይ ያለው የመዋዕለ ህጻናት ዝግጁነትን በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ይፈልጋሉ።
- አብዛኛዎቹ የ SPP ቤተሰቦች ልጃቸው መዋዕለ ሕጻናት ለመጀመር በተወሰነ ደረጃ ወይም በጣም ዝግጁ ነው ብለው እንደሚያምኑ በሪፖርት ዘግበዋል፤ ነገር ግን ዝቅተኛ መቶኛ (45%) የሚያክሉ ጥቁር ቤተሰቦች፡ ልጃቸው ከነጭ ቤተሰቦች (65%፤ ሥዕሉን ይመልከቱ) ጋር ሲወዳደር በጣም ዝግጁ ነው ብለው ያስባሉ።

> *“ተማሪዎችን በማህበራዊ እና በስሜታዊነት ጉዳይ ላይ ዝግጁ ማድረግ ከሁሉም በላይ አስፈላጊ እንደሆነ አምናለሁ። አንድ ተማሪ ራሱን መምራት፣ ጓደኛ ማድረግ እና እውነተኛ የሆነ ደግነትን ማወቅ የማይችል ከሆነ፡ የአካዳሚክ ትምህርት ክፍል ለማዳበር በጣም ከባድ ይሆናል።”*
>
> **– የ SPP መምህር**

***አብዛኛዎቹ የ SPP ቤተሰቦች ልጃቸው ለመዋዕለ ሕጻናት፣ 2023 ዝግጁ መሆኑን ማመናቸው ገልጸዋል።***



# በዘር ላይ የተመሰረተ የዕድል ክፍተቶች

## በዘር ላይ የተመሰረተ የ SPP ልጆች የዕድል ክፍተቶች ከ 2018-19 እስከ 2022-23 ዓ.ም በቅድመ ትምህርት ቤት እና በመዋለ ህጻናት ውጤቶች ላይ እንደጨመረ ያሳያል።

በዘር ላይ የተመሰረቱ የዕድል ክፍተቶች ሲባል በዘር/በጎሳ መካከል ያሉ ልዩነቶች ሲሆኑ የጥቁር ቤተሰብ ልጆች ከነጭ ቤተሰብ ልጆች ጋር ሲነጻጸሩ ዝቅተኛ የውጤት መጠን አላቸው። የግምገማ ቡድኑ በ SPP ቅድመ ትምህርት ቤቶች በየአመቱ ሶስት ጊዜ ጥቅም ላይ በሚውለው የማስተማር ስትራቴጂ GOLD (TSG) ግምገማ፣ እንዲሁም በመጀመሪያዎቹ የኪንደርጋርተን ጊዜያት ላይ በግዛቱ ውስጥ ባሉ የመዋዕለ ህጻናት ክፍሎች የሚጠቀሙበትን የ Washington Kindergarten Inventory of Developing Skills (WaKIDS) ውስጥ የዕድል ክፍተቶችን እንዳሉ ለማየት መርምሯል። [2]

- በመዋለ ሕጻናት ዘመናቸው በ TSG ላይ በቂ እድገት ያሳዩ የ SPP ልጆች የእድገታቸው መቶኛን በሚታይበት ጊዜ፡ በ 2022-23 ዓ.ም የጥቁር ቤተሰብ ልጆች ከነጭ ቤተሰብ ልጆች ይልቅ ከፍ ያለ ወይም ተመሳሳይ ደረጃ ነበራቸው፤ ይህም ከበልግ እስከ ጸደይ ባለው ዕድገት ላይ ምንም ዓይነት የእድል ክፍተት እንደሌለ ያሳያል።
- በጸደይ ወራት የነበረውን የቅድመ ትምህርት ቤት ላይ በሁሉም የ TSG ስድስት ጎራዎች[3] መስፈርቶችን ያሟሉ የ SPP ልጆች መቶኛን ስንመረምር፡እነዚህን መመዘኛዎች ከጥቁር ቤተሰብ ልጆች ይልቅ የነጭ ቤተሰብ ልጆች በበለጠ ደረጃ አሟልተዋል፤ ይህም የጸደይ ቅድመ ትምህርት ቤትን ደረጃዎች ለማሟላት በዘር ላይ የተመሰረተ የእድል ክፍተቶችን ያሳያል። እነዚህ የዕድል ክፍተቶች ከ 2018–19 እስከ 2022–23 ዓ.ም እድገት አሳይተዋል።
- በሁሉም 6 የ WaKIDS ጎራዎች የመዋዕለ ሕጻናት ዝግጁነት መስፈርቶችን ያሟሉ ልጆች መቶኛ ከ 2018–19 ጀምሮ ጨምሯል፣ ነገር ግን የእድል ክፍተቶችም ጨምረዋል። በጥቁር እና በነጭ ልጆች መካከል ያለው ክፍተት ከ5 በመቶ በ 2018–19 ዓ.ም ውስጥ ወደ 23 በመቶ በ 2022–23 ዓ.ም አድጓል (ሥዕሉን ይመልከቱ፣ የክፍተቶች ለውጦች ተጽዕኖ የደረሰባቸው በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ሊሆን ይችላል)።

***የ WaKIDS መዋለ ህጻናት ዝግጁነት ደረጃዎችን ለማሟላት በ SPP ልጆች መካከል በዘር ላይ የተመሰረተ የእድል ክፍተቶች ከ 2018-19 ወደ 2022-23 ጨምረዋል።***



# በኪንደርጋርተን ውጤቶች ላይ የ SPP ተጽእኖ

## በ 2017-18 ዓ.ም በ SPP የተማሩ ልጆች በመንግስት ገንዘብ በሚደገፈው ቅድመ ትምህርት ቤት ውስጥ ካሉ ተመሳሳይ ልጆች የበለጠ የመዋዕለ ሕጻናት ውጤት አግኝተዋል።

]በ 2017-2018 ዓ.ም በ SPP ወይም በመንግስት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ቅድመ ትምህርት ቤት ከተማሩ ተመሳሳይ ባህሪ ካላቸው ልጆች መካከል፡ በመንግስት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ቅድመ ትምህርት ቤት ከተማሩ ተመሳሳይ ልጆች ጋር ሲነጻጸሩ፡ በ SPP የተማሩ ልጆች፡ በመዋዕለ ህጻናት ከፍተኛ የትምህርት ቤት ክትትል (1.9 ከመቶ ከፍ ያለ) እንዲሁም ከፍተኛ የመዋዕለ ህጻናት ደረጃ ዝግጁነት (በተሰጠው የጥናት ጎራ መሰረት ከ16 እስከ 29 ከመቶ ከፍ ያለ) ውጤቶች አሳይተዋል።

### የተመረጡ ምክሮች

- የጥራት ማሻሻያ ስልጠና እና የአመራር ስልጠና ላይ ለመሳተፍ መምህራን ሁለቱንም የእቅድ እና የመልቀቂያ ጊዜ እንዲያገኙ ለማገዝ ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍን አስቡበት።
- በቅድመ ትምህርት ቤቶች እና ቤተሰቦች መካከል ስለ እያንዳንዱ የመዋለ ህጻናት ልጅ እድገት እና መሻሻል ለማድረግ የዝግጁነት ግንኙነትን አሻሽል።
- የዕድል ክፍተቶች ላላቸው የቡድኖች ድጋፎችን መርምር እንዲሁም የእድገት እና የክፍተቶች መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ይመረምሩ።
- የ SPP ን ተጸእኖ በቅርብ ዓመታት ውስጥ እና ከብዙ ተማሪዎች ጋር ለመረዳት ተጨማሪ ትንታኔዎችን ያድርጉ።

---

[1] በዋሽንግተን ግዛት በገንዘብ የሚደገፈው የቅድመ ትምህርት ፕሮግራም የቅድመ ልጅነት ትምህርት እና እርዳታ ፕሮግራም ወይም ECEAP በመባል ይታወቃል፣ እንዲሁም አብዛኛዎቹ ልጆች በእድሜ እና በቤተሰብ የገቢ ደረጃ (የህጻናት፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች መምሪያ) ለመሳተፍ ብቁ ናቸው [2023]። *ECEAP and Head Start*)። የግምገማ ቡድኑ በ SPP እና በመንግስት የገንዘብ ድጋፍ በሚደረግ ቅድመ ትምህርት ቤት ተመሳሳይ ህጻናትን ናሙና ለመፍጠር ከፍተኛ ግምት ያለው ቴክኒክ ይጠቀማል - ይህ ማለት ደግሞ ሁለቱ የሕጻናት ቡድኖች ተመሳሳይ የስነ ሕዝብ አወቃቀር ባህሪያት (ዘር/ብሔረሰብ፣ የገቢ ደረጃ፣ እና ቋንቋ) የነበራቸው እና የ TSG ውጤቶች ከልጁ የመጀመሪያ የቅድመ ትምህርት ዓመት በታች ነው። በናሙና ውስጥ የተካተቱት በሲያትል ውስጥ ወይም አቅራቢያ በሚገኙ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በመንግስት የሚደገፉ የቅድመ ትምህርት ቤት ልጆች ብቻ ናቸው።

[2] እነዚህ እርምጃዎች ፍጽምና የጎደላቸው ናቸው፤ ተገቢ እድገት ነው ተብሎ በሚታሰበው ነገር ላይ ባህላዊ አድልዎ ሊኖራቸው ይችላል፣ በተወሰኑ ቋንቋዎች ብቻ ነው የሚገኙት፣ እንዲሁም በአስተማሪ ትእዝብቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው (ይህም በባህሪው አድላዊነት ያለው ነው)። እነዚህ ችግሮች ቢኖሩም እንኳ፡ እነዚህ መረጃዎች የረጂም ጊዜ የልጅ እድገትን እንድንረዳ ይረዱናል።

[3] እነዚህ የ TSG መመዘኛዎች በአገር አቀፍ ደረጃ የተገመገሙ "በሰፊ የሚጠበቁ" መለኪያዎች ናቸው። በ TSG እና በ WaKIDS ውስጥ ያሉት ስድስቱ ጎራዎች ቋንቋ፣ ማንበብና መጻፍ፣ የማስተዋል እውቀት፣ ሂሳብ፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ እና አካላዊ ናቸው።